## ማስገንዘቢያ

ይህን ድረ-ገጽ ለመክፈት ያስፈለገበት ምክንያት በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በአካባቢዬ የነበሩት አብያተ-ክርስቲያናት አብዛኞች በቂ የመንፈሳዊ ትምህርት ስልጠና የወሰዱ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ያልነበራቸው ሲሆን፣ ምዕመናን እርስ በራሳቸው ይገለገሉ ስለነበር፣ ከእግዚአብሔር ቃል የተዘጋጀ ትምህርት በድረ-ገጽ ላይ ተለቆ ቢያገኙ ያግዛቸዋል በሚል ነው። ነገር ግን ማናቸውም የአማርኛ ቋንቋ ማንበብና መረዳት የሚችሉና በሌሎች እንደ እንግሊዝኛ ባሉ ቋንቋዎች የተጻፉ ትምህርቶች መረዳት የሚከብዳቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አማኞችን ጨምሮ በአረብና በማናቸውም አገሮች የሚገኙ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ያገራችን ዜጎች ሁሉ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

የትምህርቱ ዓላማ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሆኑት፣ አእምሮን በማደስ የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት ኃይል ያለውን የእግዚአብሔር ቃል በማካፈል፣ እግዚአብሔርን በማወቅ እያደጉ በክርስቶስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በራሳቸው ተስማምተው መኖር እንዲችሉ ነው።

ይህን ትምህርት ለማዘጋጀት የተጠቀምኳቸው ጥቅሶች የተወሰዱት በቢብሊካ ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር 2001፣ 2024 ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ቆየት ሲል ከታተሙት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ የተብራራ ስለ ሆነ ነው።

በአንዳንድ የትምህርት አርእስት ውስጥ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያሰፈርኩበት ቦታ አለ። ለዚህ ምክንያቱ ይኼኛው አዲሱ መደበኛ ትርጉም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ብዙዎቹ ምእመናን ላይኖራቸው ይችላል በማለት ስላሰብኩ መጽሐፍ ቅዱሱን በማፈላለግ ጊዜ ሳይወስዱ በቀጥታ ከዚሁ እንዲያገኙት በማሰብ ነው።

በድረ-ገጹ ላይ ለአዲስ ጀማሪና ለነበባር አማኞች በተመረጡ አርዕስት የተዘጋጁ ትምህርቶች ስላሉ፣ አዲሶቹ አማኞች አንዱን ርዕስ አንዴ ጀምረው ወዲያው ለመጨረስ እንዳይከብዳቸው፣ እንደ አስፈላፊነቱ በርከት ባሉ ክፍሎች በመከፋፈል በተለያዩ ቀናት ሊያነቡት/ሊያጠኑት ይችላሉ። በተጨማሪ የወንጌል ስርጭትን በሚመለከት ልምድ ለማካፈል ሁለት ትምህርቶች ተካትተዋል።

ይህን ድረ-ገጽ ከፍተው የፈለጉትን ርዕስ መርጠው በውስጡ የሰፈረው ትምህርት ሲያነቡ፣ ሙሉውንም ሆነ ከፊሉን ትምህርት ኮፒ አድርጎ በማስታወሻ መያዝ ወይም ለሌሎች ማስተላለፍ ከፈለጉ የተፈቀደ ነው።

በዚህ ድረ-ገጽ አሁን የተለቀቁትና ወደፊትም የሚጨመሩት ትምህርቶች ሁሉ አዘጋጅ ስሜ **ዶ/ር ኤልያስ ታሪኩ** ሲሆን፤ የወንጌላዊያን አማኞች መሰረታዊ የእምነት መግለጫዎች እና መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ዘመን ይሰራ እንደነበረው አሁንም እንደሚሰራ የማምን፣ ከ1989 ዓ. ም. ጀምሮ በእንስሳት ሕክምና በተለያዩ አካባቢዎች እየተተዘዋወርኩ ስሰራ በነበረበት ጊዜ ሁሉ የምስራቹ ቃል አገልግሎት ሳበረክት የቆየሁ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ነኝ። ክብሩ ለጌታ ይሁን፥ አሜን!!